# <u>እንዴት ይሆን ?</u>

ያደነዝዛል ወይ ያፈዛል ?
ወይስ እንደቆየ ቁስል እያደር ይጠዘጥዛል ?
እንደ እናት ሞት ሌት ተቀን ይቆረቁራል ?

*ህልም ሲሞት ምን ይሰማል ?*

እየዋለ እያደረ እየደከመ ይሄዳል ?
ያለዚያስ ዘመን . . . ሲገፋ ስቃይ ህመሙ ይበዛል ?

ወይስ እንደነቀርሳ . . .
ባጥንት ውስጥ ገብቶ ያጋያል ?
እንቅልፍ ነስቶ ሌሊቱን . . .
በቅዠት አንቆ ያረዝማል ?

በበቀል እየቀጠቀጠ . . . አንካሳ አድርጎ ያስቀራል ?
ወይስ እንደ ጎርፍ ከብቦ . . . ኑሮን በቁጭት ያደርቃል ?

*ህልም ሲሞት ምን ይሰማል ?*

እንደ ጀንበር ሆድ እያባባ . . .
ካድማስ ባሻግር ይጠፋል ?
ወይስ እንደ ውሃ እያሳሳቀ . .
ህልምም ወደሞት ይነዳል ?

ህይወት እንዳልበረዉ . . .
ትንፋሽ እንዳልነበረው . . .

ይሞቅ እንዳረነበረ
ይስቅ እንዳልነበረ
በእግሮች ሮጦ በክንፎቹ እንዳልበረረ

ሮጦ እንዳላስሮጠ
ምጦ እንዳላስማጠ
ነፍስን በጉጉት ኮልኩሎ .... ድንበር እንዳላስቧረጠ

አባትን እናትን . .  አገርን ሁሉ አስክዶ
ጨርቅ አስጥሎ . . አሳብዶ

እንዳላስከነፈ ብርቱውን
ነፍስን በተስፋ ሞልቶ እንዳላፈጠነ እግርን

የወጠኑት የለፋለት . . .
<u>ገ</u>ዝ ንብረት ጥለው የጠፋለት . .
እንደ ጣኦት አክብረው.... አይን ከድነው ያመለኩት

እንደ ነፍሰ ጡር ተስፋ
ቀናት የቆጠሩለት
እንደ አዲስ ሙሽራ በጉገት የደከሙለት

ሲክቡት የኖሩት ሁሉ
ህልምና ተስፋ ሲሞት . . .
ተስፋ እንደአ<u>ባ</u>ራ ተበትኖ
ሲጠፋ ዳግም ላያዩት

*ህልም ሲሞት ምን ይሰማል ?*

ወይስ በነገ ተስፋ . . .
ወጌሻ ታሽቶ ይድናል ?
ጊዜ መድሃኒት ሆኖት . . .
በእግርቹ ጸንቶ ይቆማል?

እንደገና ይነሳና . . .
በትንሳኤ ይታደሳል ?
እንዳራስ ባጥሚት ጠንክሮ . . .
ዳግመኛ ነፍስን ይዘራል ?

ይታደስና ህልምም . . .
እንደ አደይ አበባ ይፈካል ?
ሺህ አፍርቶ ሺህ አብልቶ . . .
የኑሮን ጠኔ ያበርዳል ?

ይስቃል ይፈነድቃል ?
ይነሳል ዳግም ይድሃል ?
ይሮጣል ይንደረደራል ?
ወይስ በፊቱ ወድቆ ተደፍቶ በዚያው ይቀራል ?

እንደቆሰለ አውሬ . . .
በገዛ ደሙ ይሰክራል ?
በገዛ እጆቹ ታንቆ . . .
የገዛ ሞቱን ይሞታል ?

እድሜ ገፍቶ . . .
ጉልበት ላልቶ . . .
ጸጉር ሸበቶ . . .
መላ ጠፍቶ . . .

ዝብርቅርቁ ይወጣል ?
እንደ አሮጌ ጋቢ ድሩ ይጎለጎላል ?

መበራቱ ድንገት ይጠፋል ?
ትንፋሽ ይቀዘቅዛል ?
መጋረጃምውም ይዘጋል ?

*ህልም ሲሞት ምን ይሰማል ?*

ስሜቱስ ከቶ እንዴት ነው . .
የገዛ ራስ ህልም ሲቀበር ?
የብርሃኑ መሰረት . . .
የኑሮ ፋኖስ ሲሰበር ?

**ዘውዱ ሳህሉ**
October 12 , 2007

***Back to Meskot***

---

***The views reflected in the above poem/article are solely of the author and are not necessarily shared by*** *Meskot****. You may contact Zewdu Sahlu  for comments at*** *zewdu_michael@yahoo.com*